بسم الله الرحمن الرحيم

የኢትዮጵያ ፌ/ዴ/ሪ/ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL

Addis Ababa
Ethiopia

المجلس الأعلى للشئون الإسلامية في
جمهورية اثيوبيا الديموقراطية الفيدرالية
اديس أبابا
اثيوبيا

አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ

ቁጥር ጠ/ም/1883/65/2000
ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ለደህንነት፣ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- የትምህርት ሚኒስቴር የአምልኮ መመሪያ አሁን ባለበት መልኩ እንዳይጸድቅ እንቅፋት የሆኑትን አካላት ይመለከታል፡፡

በአዲሱ ሚሌኒየም ሀገራችንን ወደ ተሻለ እድገት ለማሸጋገርና ህዝቦቿ በመቻቻል የኅሊም ተምሳሌት ሆነው እንዲቀጥሉ በመንግስት ጥረት እየተደረገ መሆኑ ይታመናል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ7/5/1999 ዓ.ም በስምምነት ላይ በተደረሰው መሠረት የትምህርት ሚኒስቴር የአምልኮ ሥርአትን የሚመለከት መመሪያ ማዘጋጀቱ ይታወቃል፡፡ ሆኖም መመሪያው እንዳይጸድቅ እንቅፋት እየሆኑ ያሉ አካላት መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡በዋንኛነት የክልል 14 አስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት፣አንዳንድ የወሃቢዮች ድርጅቶች እና በሀቡሰ ወረቀት በመጠቀን ህዝበ ሙስሊሙን እየቀሰቀሱ ያሉ ጥቂት ጽንፈኞች ይጠቀሳሉ፡፡ ስለዚህ ይህ መመሪያ ሳይሻሻረና በሥራ ላይ እንዲዉል አስፈላጊ እርምጃዎች ካልተወሰዱ በቀር መመሪያው እክል ሊገጥመው እንደሚችልና በጠቅላይ ምክር ቤታችንም ላይ አሉታዊ ስሜትን ሊፈጠር እንደሚችል እሙን ነው፡፡ ህብረተሰቡን ከማረጋጋት አንስቶ ጸረ-ሰላም የሆኑትን እስከ መልቀም ያለ አፋጣኝና ተገቢ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ያለዚያ ጉዳዩ ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን ስለሚችል ከዚህ በታች ያሉ ነጥቦች በአፋጣኝ ቢተገበር መልካም ነው፡፡

ሀ) ሙስሊሙን የማረጋጋት ሥራ ጊዜ ሊሰጠው አይገባም፡፡

ለ) ነገሩን ሁሉ በማራገብና በማናፈስ ሕዝበ ሙስሊሙን ለሁከት እየቀሰቀሱ ያሉትን ኔል-ቴዴስና ሠሰፊያ የተባሉ ጽንፈኛ ጋዜጦችን ለጊዜው ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸውና ጉዳዩ ከረገበ በኋላ ፈቃዳቸው እንዲነጠቅ፡፡

ሐ) በየመስጊዱ ወረቀቶችን የሚበትኑትን ጽንፈኞች ለማደን የተጠናከረ ክትትል እንዲደረግ፡፡

መ) በአዲስ አበባ መጅሊስ የተቋቋመው ኮሚቴ እንዲበተንና ኩተግባሩ እንዲቆጠብ ማድረግ፡፡

የኢትዮጵያ አስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት መመሪያው እንዲፋጠር የሚያደርገውን ያለለሰ ጥረት ዳግም እያረጋገጠ ከላይ በተጠቀሱት አካላት ላይ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩን ለጊዜው ካረጋጋን በኋላ ስወ ሲዘጋጋ ቢጸድቅ መልካም ነው የሚል ጽኑ አምነት እንዳለው በትህትና ይገልጻል፡፡

<u>ግልባጭ</u>

- ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን
- ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን
- ለትምህርት ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለሁሉም ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽኖች

<u>በያለበት</u>

ከሰላምታ ጋር

ዲያ ኸሊፋ ራሽዲ ሰይድ
Sheikh Khalifa Rashidi Seid
ምክትል ፕሬዚዳንት
Vice President
نائب رئيس

Tel 725965 | ስልክ ቁ. 725965 | الهاتف 725965
P.O. Box 2844 | ፖ.ሣ.ቁ 2844 | ص ب 2844
Fax No 725966 | ፋክስ ቁ. 725966 | فاكس 725966